# ዴሞክራሲያ

*****************************************************

* የኢትዮጵያ ሕዝባዊ አብዮታዊ ፓርቲ (ዴሞክራሲያዊ) ልሣን*

*****************************************************

ቅጽ 33 ቁጥር 3 ሐምሌ 2000 ዓ. ም.


## መሐሉ ዳር ሳይሆን

ኢሕአፓ የተመሰረተበትን 36ኛ ዓመት በምናከብርበት በአሁኑ ወቅት ለድርጅቱ መመስረት ምክንያት የነበሩትን ዋና ዋና የአገሪቱን ችግሮች መለስ ብለን እየመረመርንና እየተባባሱ የመጡ ሁኔታዎችን በጥሞና እያስተዋልን እንዲሁም ለሕዝባችን ሰቆቃ ማብቂያውን መንገድ ከመፈለግ ለአፍታም ባለመዘናጋት ጭምር ነው:: ቀደምት የነበሩትን የኢኮኖሚ የፖለቲካና የማኅበራዊ ኑሮ ችግሮች ለማስወገድ የተደረጉትን ትግሎችና የተከፈሉትን መስዋዕትነቶች ዛሬ ከሠላሳ ስድስት ዓመታት በኋላ መለስ ብለን ስንቃኝ ልባችን እጅጉን ይደማል:: ለዚህም ዋነኛው ምክንያት የትግሉ ዋነኛ ባለቤት የኢትዮጵያ ሕዝብ ዛሬም ከመከራ አዘቅት ውስጥ ሆኖ የድረሱልኝ ጥሪውን ከፍ አድርጎ በማሰማት ላይ መሆኑ ነው::

እርግጥ ነው፥ ባለፉት ሠላሳ ስድስት ዓመታት የፖለቲካ ስርዓት ለውጦች በአገራችን በኢትዮጵያ ውስጥ ተከስተዋል:: ከአጼያዊ (ባላባታዊ) ሥርዓት ወደ ወታደራዊ አምባገነን ሥርዓት ተሸጋግረናል፤ ለጥቆም ወደ ጎሳዊ ክልልተኛና አሸባሪ ቡድን አገዛዝ ገብተናል:: ኢሕአፓ ግንባር ቀደም ሆኖ ራሱንም ሕዝቡንም በማደራጀት መቀየር እንዳለባቸው ያመነባቸውና የታገለላቸው የአገራችን የኢኮኖሚ የፖለቲካና የማኅበራዊ ችግሮች እያደር ወደ አዘቅት ማሽቆልቆላቸው ዛሬ የማንክዳቸውና የማይታበሉ ሃቆች ሆነዋል:: አያሌ ኢትዮጵያውያን ውድ ህይወታቸውን ለተሻለች ኢትዮጵያ መገንባት በግንባር ቀደምትነት የመስዋዕትነትን ክቡር ዋጋ ቢከፍሉም ዛሬም እንደገና ከድሮው በባሰ መልኩ፥ አገራችንና ሕዝባችን ማለቂያና ማቆሚያ ለሌላቸው ሦስት አስከፊ አደጋዎች ተጋልጠውና ተመቻችተው ይገኛሉ:: አንደኛው፥ በሰሜናዊው የኤርትራ ክፍለ ሀገራችን በኩል ሃገራችን ላይ የደረሰባት የጥቃት ቁስል ሳይደርቅላት፥ ለሌላ አዲስ በደልና ጥቃት በምዕራባዊው የድንበር ግዛቶቿ በኩል የመጣባት መሆኑ፤ ሁለተኛው፥ ምናልባት ካሁን ቀደም ከምናውቃቸው የረሃብ መልኮች በባሰ ደረጃ (የ1977ቱን ጨምሮ) ህዝባችን ለሌላ ከፍተኛ የረሀብና የጠኔ አደጋ እየተጋለጠ መምጣቱ፤ ሦስተኛው፥ ካልተወረረች በስተቀር ሃገራችን ገጥሟት በማያውቅ ውጫዊና አካባቢያዊ ጦርነት መጠመዷ ናቸው:: እነኝህ ሦስት አደጋዎች ተዳብለው ያሉባት አገራችን ምናልባትም ትናንት ከትናንት በስቲያ ከአያት ከቅድመ-አያቶቻችን እንደተረከብናትና ነግ ከነገ በስቲያ እንደነበረች ሆና ላትቆየን ትችላለች፤ ሕዝባችንም ባልፈቀደውና ባላሰበው የጦርነት አውድማ ሊማገድ ይችላል - በተለይም የፖለቲካ ድርጅቶች ኃላፊነቱ ካልተሰማቸውና በፍጥነት ለተግባራዊ ምላሽ በጋራ ካልተነሱ በስተቀር::

ቅድሚያ ለሃገርና ለሕዝብ ብለን ተነስተናልና በዛሬው የዴሞክራሲያ እትማችን በቅርቡ የህወሓት/ኢሕአዴግ አገዛዝ በተለይ ከጎንደር ሰሜናዊ ምዕራብ እስከ ጋምቤላ ኢሉባቦር ያለውን የኢትዮጵያ ለም መሬት ለሱዳን አሳልፎ የመስጠት ከፍተኛ የሃገር ክህደት ላይ ልዩ ትኩረት ለማድረግ ተገደናል:: በመሰረቱ ህወሓት/ኢሕአዴግ ለኢትዮጵያና ለኢትዮጵያውያን ቅንጣት ታህል ደንታ እንደሌለው በገዛ ራሱ ተደጋጋሚ እኩይ ተግባራት ያረጋገጠው ገና ራሱን ይፋ እንዳደረገ ነው:: በተለይም ህወሓት ለኢትዮጵያ ግዛታዊ አንድነትና ብሄራዊ ሉዓላዊነት መጠበቅ ሳይሆን ዓላማዬ ብሎ የተነሳው የትግራይ ነፃ ሪፑብሊክን ለመመስረትና ከኢትዮጵያ ለመገንጠል እንደሆነ እንደሃገራችን አቆጣጠር በ1968 ዓ/ም በጻፈውና ባሰራጨው ማኒፌስቶው ላይ በግልፅ አረጋግጧል:: ኢትዮጵያዊውን የትግራይ ህዝብና የኢትዮጵያ አካል የሆነችውን የትግራይ ክፍለ ሀገር ከኢትዮጵያ ለመገንጠል የተመሰረተው ይህ ድርጅት ለኢትዮጵያ ግዛታዊ አንድነትና ብሄራዊ ሉዓላዊነት ይቆማል ብሎ ማሰብ ጨርሶ የዋህነት ነው:: የህወሓት/ኢሕአዴግ ቁንጮ መለስ ዜናዊ "ምኒልክ በሰይፍና በጎራዴ ለመሰረቱት ድንበር ዘብ አንወጣም" በማለት ሲሳለቅ በተደጋጋሚ መደመጡም ለዚህ አንድ ተጨማሪ ማስረጃ ነው::

ህወሓት እንደ ድርጅት ኢትዮጵያንና ኢትዮጵያዊነትን በሚጠሉ ፀረ-ኢትዮጵያ ግለሰቦች የሚመራ ድርጅት ለመሆኑ አያሌ ማስረጃዎች ማቅረብ ይቻላል:: የድርጅቱ መሪዎች ለኢትዮጵያ ካላቸው ጥላቻና እኩይ ምኞት በብዙ ሺህ የሚቆጠሩ የትግራይ ወጣቶችን በኤርትራ በረሀዎች ከሻዕቢያ ጎን በማሰለፍ አስፈጅተዋል:: "ኤርትራ በኢትዮጵያ በቅኝ ግዛትነት ተይዛ ብዙ የተጎዳችና የተበደለች አገር ነችና ሙሉ ነፃነቷን ማግኘት አለባት" በማለት የተባበሩት መንግስታት ድርጅትንና የውጭ መንግስታትን በማስጨነቅ ኢትዮጵያን ክፉኛ በሚጎዳ መልኩ ኤርትራን ከኢትዮጵያ ያስገነጠለም ድርጅት ነው:: የበላይ ጠባቂው የሆነው የአሜሪካ መንግስት እንኳን ቢማጸነው÷ በአሻፈረኝ ኢትዮጵያን ያለምንም የባህር በር ያስቀረና ለዘለዓለማዊ የኤኮኖሚና የጸጥታ ችግር የዳረገ÷ በቀጣይነት በፀረ-ኢትዮጵያ ዓላማ ዛሬም ድረስ የሚንቀሳቀስ ድርጅት ነው:: እዚህ ላይ በቅርቡ ከሻዕቢያ ጋር ባደረገው ጦርነት እንኳ በሁለቱም በኩል ከመቶ ሺህ በላይ የሚቆጠሩ ዜጎች ካለቁ በኋላ አገኘሁ ያለውን "ድል" ፉርሽ አድርጎ የአስመራውን የአቶ ኢሳይያስ አፈወርቂን "መንግስት" ለማዳን ለእርቅ ስምምነት ወደ አልጀርስ የሮጠበትን የክህደት ተግባሩን ማስታወሱም እጅግ ጠቃሚ ነው:: በዚያም ሳያበቃ÷ በርካታ አገር ወዳዶችና የታሪክና የህግ ምሁራን ኢትዮጵያ ያልተቀበለቻቸውንና ሁለተኛው የጣሊያን ወረራ ህጋዊነት ያሳጣቸውን የውል ሰነዶች ይዞ ወደ ዓለም ፍርድ ቤቱ የኢትዮ-ኤርትራ ድንበር ኮሚሽን መሄዱ ኢትዮጵያን የሚጎዳ መሆኑን እየነገሩት አሻፈረኝ በማለት ለሻዕቢያ መንግስት የሚያደላ ብያኔ እንዲወሰንም አድርጓል:: ለጊዜያዊ የፖለቲካ ጥቅም ሲል ብያኔውን አልቀበልም እያለ ቢያንገራግርም 70 ኪሎ ሜትር ካሬ ለም መሬት ከኢትዮጵያ ሰሜናዊ ምዕራብ ክፍል ቆርሶ አሁን በቅርቡ ለሻዕቢያ ለመስጠት እየተዘጋጀ መሆኑንም የውስጥ አዋቂዎች እየተናገሩ ነው:: እኒህንና ሌሎችንም ኢትዮጵያን የሚጎዱ ብዙ የክህደት ተግባሮችን የፈጸመ ይህ ድርጅት የሚመራው አሸባሪ መንግስት ነው ዛሬ ከሰሜናዊ ምዕራብ የጎንደር ክፍለ ሀገር አንስቶ እስከ ጋምቤላ ኢሉባቦር ድረስ ያሉትን የኢትዮጵያ ለም የእርሻና የደን ልማት መሬቶች ለሱዳን አሳልፎ የሰጠው::

እዚህ ላይ ህወሓት ለምንድን ነው በአጼ ኃይለ ሥላሴም ይሁን በደርግ መንግስታት ዘመን የተከበረውን ምዕራባዊውን ወሰናችንን ያስደፈረውና ለሱዳን በችሮታ የለገሰው? የሚል መሰረታዊ ጥያቄ መነሳቱ አይቀሬ ነው:: ሱዳን እንደ ፈረንጆች አቆጣጠር በ1958 ነፃነቷን ከእንግሊዝ ካገኘች በኋላ በአጼ ኃይለ ሥላሴ ዘመነ መንግስት ወቅት ከኢትዮጵያ ጋር ያላትን የድንበር ችግር ያነሳችው አንድ ጊዜ ብቻ ነው:: ይህም በ1971 ዓ/ም ሲሆን ጥያቄውም የተነሳው የሴቲት ሁመራን አካባቢ ብቻ የሚመለከት ነበር:: የአጼ ኃይለ ሥላሴ መንግስትም በሰላማዊና በዲፕሎማሲያዊ መንገድ ሱዳን ጥያቄዋን እንድታነሳና በመልካም ሰላማዊ ጉርብትና እንድትቀጥል ለማድረግ ጥሯል:: ሙሉ በሙሉ ምክንያቱ ይህ ብቻ ነው ባይባልም አጼ ኃይለ ሥላሴ በ1972 ዓ/ም የደቡብና የሰሜን ሱዳን የእርስ በርስ ጦርነት

እንዲቆም የተጫወቱት የሽምግልና ሚናና የተገኘው የሰላም ስምምነት የዚሁ የድንበር ስምምነት አንድ መግለጫ ነበር ለማለት ይቻላል:: በደርግ ዘመን ህወሓት ወደ ጎንደር ከዘለቀና ደርግ ከኢሕአፓና ከህወሓት ጋር ባደረገው ጦርነት ተዳክሞ የጎንደር ምዕራባዊ ክፍሎችን መቆጣጠር እስኪያቅተው ድረስ÷ ሱዳን የድንበር ጥያቄ አንስታ አታውቅም:: ይልቁንም ጀብሀን ሻዕቢያንና ህወሓትን በጣም ትረዳ ስለነበረ ከዛሬ ነገ በደርግ ወታደር ልወረር እችላለሁ ብላ ትሰጋ ነበር:: የኋላ ኋላ ህወሓት ከወልቃይት እስከ ጃኖራ ያለውን የጎንደር ቆላማና ምዕራባዊ ክፍል ሲቆጣጠር፣ ሱዳን በታያ ግንባርና በሽንፋ ወንዝ በኩል ወደ ኢትዮጵያ ግዛት ለመዝለቅና አካባቢው የሚለግሳቸውን የተፈጥሮ ሀብቶች የራሷ ለማድረግና ለመጠቀም ሞክራለች:: በዚህን ወቅት ነበር  አካባቢውን የሚቆጣጠረው የኢሕአፓ ሰራዊት የሱዳንን ወታደራዊ እርምጃ የመከተውና የመለሰው:: በዚህ ወታደራዊ ግጭት ወቅት ኢሕአፓ የተወሰኑ ታጋዮቹ ቢሰውበትም የበለጠ ጉዳት በሱዳን ወታደሮች ላይ አድርሶ ጥቃቱን በታላቅ ጀግንነትና አርበኝነት ተከላክሏል:: ህወሓትስ?

ህወሓት ለስልጣን ከመብቃቱ በፊት በብዙ መልኩ የሱዳን መንግስት ተጠቃሚ ነበር - በተለይም ወልቃይትን ከተቆጣጠረ በኋላ:: በዚህን ወቅት በተለይ ከወልቃይት እስከ ፖርት ሱዳን ድረስ ሙሉ የእንቅስቃሴ መብትና ትብብር ከወቅቱ የሱዳን መንግስት አግኝቷል:: የሱዳን የፀጥታ ባለስልጣናት ከህወሓት መሪዎች÷ በተለይም ከመለስ ዜናዊ÷ ጋር በጠበቀ የጥቅም ግንኙነት ተሳስረውም ነበር:: ህወሓት ከአሜሪካ ጋር መወዳጀት ከጀመረበት ጊዜ አንስቶ ደግሞ ከሱዳን ጋር የሦስት ጎንዮሽ ግንኙነት (ህወሓት/ሻዕቢያ-አሜሪካ-ሱዳን) አድርጓል:: ከጥቃቅን የጋራ ስምምነቶችና ተግባሮች ባሻገር እስከ ጣምራ ወታደራዊ እንቅስቃሴዎች ድረስ ተረዳድተዋል:: ህወሓት የመጨረሻውን ወታደራዊ ጥቃት በኢሕአፓና በደርግ ላይ በሚወስድበት ጊዜ በምዕራብ ግንባር ሙሉ ወታደራዊ ድጋፉን ከእግረኛ እስከ ታንከኛ ድረስ ያገኘው ከሱዳን መንግስት ነው:: ይህ ያልተቆጠበ ድጋፍ ደግሞ ህወሓትን የሱዳን ዘላለማዊ ባለዕዳ አድርጎታል::

ህወሓት ዛሬም የሱዳንን ወዳጅነት አጥብቆ ይፈልጋል - ሱዳን ከምትፈልገው በላይ:: ሱዳን ከኢትዮጵያ ጋር የሚያዋስናትንና ህወሓት እንደ ፖለቲካ መሳሪያ ሊጫወትበት የሚሻውን የደቡብ ሱዳን ችግር ለጊዜውም ቢሆን ተቆጣጥራለች:: በዳርፉር በኩል ያለው የሱዳን ችግር በርቀት ምክንያት ለህወሓት ይህንን ያህል ፖለቲካዊ ጠቀሜታ አይሰጠውም:: በአንጻሩ ግን÷ ሱዳን ከኤርትራ ጋር ትጎራበታለች:: ሱዳን ለኢትዮጵያ ተቃዋሚ ኃይሎች ጭምር  መንደርደሪያና መገልበጫ ነበረች፣ አሁንም ልትሆን ትችላለች ህወሓትን ለመጉዳት ከፈለገች:: ሱዳን ለህወሓት መዳኛም መጥፊያም ነች ለማለት ነው:: በሌላ በኩል ዛሬ ህወሓት በሁሉም አቅጣጫ እንዲህ ተወጥሮ ባለበት ሁኔታ ከሱዳን ጋር ለመጋጨት ፈጽሞ አይቻለውም÷ አይሞክረውም:: ስለዚህም ሱዳን ከኢትዮጵያ ለማግኘት የምትፈልጋቸውን ነገሮች በሙሉ በቀላሉ ለማግኘት የምትችለው አሁን ነው:: እነኝህ ምክንያቶች ናቸው፣ ከህወሓት ለኢትዮጵያ ዳር ድንበር ግድየለሽነት ጋር  ተዳምረው፣ ዛሬ በምዕራባዊው የወሰን ክልላችን በኩል ለተሰነዘረብን ጥቃት ያጋለጡን::

ሱዳን ከኢትዮጵያ የምትፈልጋቸው የተፈጥሮ ሀብቶች ለራሷ ለሱዳን መኖር አለመኖር ጭምር መሰረታዊ ናቸው:: የውኃ ሃብቶቻችንን በብርቱ መጠቀም ትፈልጋለች:: ዓባይ ወንዝ ዓለም አቀፋዊ ገጽታ አለውና የወንዙ ተፋሰስ አገሮች ደህንነት የሁሉም ችግር ነው:: ሱዳን ከገቡ በኋላ አትባራ በመባል የሚታወቁት የጓንግና የባህረ ሰላም (አንገረብ) ወንዞቻችን ለሱዳን የመጠጥ ውኃና ለእርሻ እድገት በጣም አስፈላጊዎች ናቸው:: እኒህ ሁለት ወንዞቻችን ከደጋው የጎንደር ክፍል ተነስተው በቆላማዎቹ መተማና አብደራፊ በኩል ወደ ሱዳን ይፈሳሉ:: እነኝህንም የውኃ ሃብቶች መቆጣጠር የሱዳን የዘወትር ፍላጎት ነው:: ባሁኑ ወቅት ሱዳን ጓንግን ተሻገራ ወታደሮቿን  አስፍራለች÷ ህወሓትም መርቆላታል:: ከዚህ በተጨማሪ የምዕራባዊው ድንበራችን ቦታዎች ለእርሻ ልማት  ከመመቸታቸውም በላይ የሚበቅሉባቸው ዛፎችና የቀርከሀ ተክሎች ለሱዳን የመኖሪያና የማከማቻ ቤቶች ስራ በጣም አስፈላጊዎች ናቸው:: ስለዚህ በአብዛኛው ምድረበዳ የሆነችው ሱዳን የኢትዮጵያን ለም መሬቶች ብትመኝ

ከቶውንም አያስደንቅም። የሚገርምና የሚደንቀው ለገዛ ሃገሩ ሳይሆን ለጎረቤቶቹ ወይም ለሌላ ለቆመ በዚህም ሳቢያ ለግል ጥቅሙ ቅድሚያ ለሚሰጥ መንግስት ተብዬ ስርዓት መታደላችን ነው!

የህወሓት/ኢሕአዴግ የምዕራባዊውን ክፍል ድንበራችን አለማስጠበቅና የሱዳን ይህንኑ የድንበራችንን መሬት መመኘት ተደራራቢና ተደጋጋፊ ሆነው ያጎሉት አንድ ሃቅ ቢኖር ህወሓት/ኢሕአዴግ ምንጊዜም ኢትዮጵያን ለከፍተኛው ተጫራች ለመሸጥ ወደኋላ የማይል ከሀዲ፥ አገር በቀል ፀረ ኢትዮጵያ ኃይል መሆኑን ነው። ለዚህም ነው በቅርቡ በስውር የተፈራረመውን የድንበር ውልና ስምምነት ከኢትዮጵያ ሕዝብ ጀርባ ተሰውሮ በመፈፀም ያለምንም ፀፀት ቆርሶ ለሱዳን የሰጠው። በበርካታ አገር ወዳዶች ጩኸትና በሱዳን ጋዜጣዎች ላይ ይፋ ባይወጣ ኖሮ ከሀዲው ህወሓትና መሪው መለስ ዜናዊ ጉዳዩን ከኢትዮጵያና ከዓለም ሕዝብ ደብቀው ለማቆዬት ነበር እቅዳቸው። የኢትዮጵያን መሬት አሳልፈው ሰጥተው፥ በሥፍራው የነበሩትን የኢትዮጵያ ዜጎች አፈናቅለው፥ ለክብራቸውና ለመሬታቸው እምቢኝ ያሉትን ጀግኖች ኢትዮጵያውያኖች በሱዳን ወታደር አስገድለውና አሳስረው "ኢትዮጵያ ከሱዳን የነጠቀችውን መሬት ብቻ ነው የመለስነው እንጂ ምንም አሳልፈን የሰጠነው መሬት የለም " በማለት ለመሸፈጥ ሞክረዋል፥ እርስ በርሳቸው የተቃረኑ መግለጫዎችንም አውጥተዋል።

በተከታታይ ህወሓት/ኢሕአዴግ በኢትዮጵያና በሕዝቧ ላይ የፈጸማቸው ክህደቶችና በደሎች የሚያመለክቱት ለኢትዮጵያ ዳር ድንበር መጠበቅ ቅንጣት ታህል ግድ የሌለውና ከኢትዮጵያ ብሄራዊ ሉዓላዊነት ይልቅ የግል ጥቅሙ የሚበልጥበት መሆኑን ነውና በዚህ ላይ ከቶውንም ብዥታ መኖር የለበትም። ህወሓት ኢትዮጵያንና ኢትዮጵያዊነትን መልሶ ለመውጋት የተፈጠረ ፀረ ኢትዮጵያ ኃይል ነው። እንደነዚህ ዓይነት መንግስቶች ደግሞ በአንድ አገር ላይ ያላቸውን የኤኮኖሚና የፖለቲካ ቁጥጥር ይዘው ለመቆዬት ሲሉ አገርና ሕዝብን በማያቋርጥ ጦርነት ውስጥም መክተት ልዩ ባሕርያቸው ነው። ይህንን ሁኔታ ለማስፋፋትም ከድንበራቸው አልፈው ከአቻ የፖለቲካ ወዳጆቻቸው ጋር በስውር ይስማማሉ። ህወሓት ከሱዳን ጋር በማድረግ ላይ ያለው የድንበር ማካለልና በአካባቢውና ሌሎች አጎራባች ሃገሮች ጋር የጫራቸው የጦርነት እሳቶች የዚህ ዓይነቱ የፖለቲካ ክስተት መግለጫዎች ናቸው። ሕዝባዊ መሰረት የሌላቸው የህወሓት/ኢሕኤዴግ ዓይነት መንግስታት ሌላው የመለያ ባሕሪያቸው ማጣፊያው ባጠራቸው ወቅት የአጥፍቶ መጥፋት ቅድመ ዝግጅት ማድረግ ነው። ህወሓት/ኢሕአዴግም መግዛት ሲሳነውና የኢትዮጵያን ንብረቶች መቦጥቦጥ ሲያቅተው አገሪቱን በትኖ ለመጥፋት መዘጋጀቱን የራሱ ሕገ-መንግስት በተለይም አንቀጽ 39 ገሃድ ካደረገው ዓመታት ተቆጥረዋል። ስለሆነም አገዛዙ ከኢትዮጵያ ሕዝብ ጋር ደመኛ በመሆኑ ለዳር ድንበራችን ዘብ መቆም የሚጠበቅበት አይደለም፤ አይሆንም - ይልቁንም በእኩይ ድርጊቱ በመቀጠል ወደፊትም ሌሎች ድንበሮቻችንን እንዲቀራመቱ መጋበዙ አይቀሬ ይመስላል።

አሁን እያስቆጣን ያለውና በሱዳንና በሃገራችን ምዕራባዊ ድንበር የተከሰተው የህወሓት ከፍተኛ ሃገራዊ ወንጀል የኢትዮጵያዊያንና የኢትዮጵያ ሀቀኛ የፖለቲካ ድርጅቶችን ሁሉ በር ያንኳኳ መሰረታዊ ጉዳይ ነው። በመሆኑም ነው ኢሕአፓ (ዴ) በተጠቀሰው ምዕራባዊው የድንበር መሬታችን ጉዳይ ላይ ቀደም ብሎ ሚያዝያ 9 2000 ዓ/ም ድርጅታዊ መግለጫ በማውጣት በጉዳዩ ላይ ተግባራዊ አፋጣኝ ምላሽ እንዲሰጥ የጋራ ጥሪ ያደረገው። በታሪካችን በተለያዩ ወቅቶች ተደጋግሞ እንደታየው የኢትዮጵያ ሕዝብ ለዳር ድንበሩ ተከብሮ መኖርና ለእናት ሃገሩ ሉዓላዊነት መጠበቅ ለመታገልና አስፈላጊውን መስዋእትነት ለመክፈል ሁሌም ዝግጁ ነው። ኢትዮጵያን በጨለማውና በቅኝ ግዛት ዘመን ሳይቀር ብቸኛዋ ነፃ አገር እንድትሰኝ ያስቻላት የሕዝቧ ጀግንነትና አልደፈር ባይነት ነው። ዛሬ ግን በነፃነትዋ ታፍራና ተከብራ ለዘመናት የኖረችው አገራችን ቅንጣት ታህል የዜግነት ግዴታ በማይሰማው ከሀዲ የፖለቲካ ድርጅት መዳፍ ስር ወድቃለች። በሚጠላትና ሊያጠፋት በተዘጋጀ መንጋ ከሀዲና የባንዳ ጥርቅም ልትተዳደርም በቅታለች። ይህ ሳያንስ ሊቀራማመቷት በሚመኙ ውስጣዊና

ውጫዊ ኃይሎችም ተወጥራለች። ታድያ አገርንና ሕዝብን ለማዳን በጋራ እንነሳ የሚለው ጥሪ ከመፈክር ባሻገር በተግባር መተርጎም አለበት።

በመሰረቱ አገርና ሕዝብን ማዳን ማለት ለዳር ድንበራችን ዘብ እንቁም፣ ከቀዳሚዎቹ ጀግኖቻችን የተረከብናትን ነፃ ሃገር ሳትሸራረፍ ወይም ሳትቆራረስ ለቀጣዩ ትውልድ እናስረክባት፣ አሁን ደግሞ በተለይም በጠረፍ አካባቢ የሚኖረውን ሕዝባችንን እንደግፍ፥ እናስተባብር፥እናደራጅ አብረንም የጋራ ሃገራችንን ከውጭ ጥቃት እንጠብቅ ማለት ነው። አገርንና ሕዝብን ማዳን ማለት ሕዝባችንን እየተዘጋጀለት ካለው የጦርነት እልቂት እናትረፈው ማለት ነው። አገርንና ሕዝብን ማዳን ማለት አገርንም ሕዝብንም ከመከፋፈል፥ ከመቆራረስና ከጥፋት እናትርፍ ማለት ነው። ስለሆነም ከእንግዲህ ወዲህ ኢትዮጵያዊያን ሁሉ በሰንካላ ምክንያቶች መታለልና ዳተኝነት ማሳየት አይኖርባቸውም። **ባሁኑ የህወሓት/ኢሕአዴግ አያያዝ መሐሉ ዳር ሳይሆን ቀድሞ መገኘት ያስፈልጋል።** ስለሆነም ሁሉም ኢትዮጵያዊ ዜጋ፥ ሁሉም ኢትዮጵያዊ ድርጅት “አገርንና ሕዝብን ማዳን” ለሚለው ወቅታዊ ጥሪ ተግባራዊ ምላሽ መስጠት መቻል ይኖርበታል - እዬዬም ሲደላ ነውና።

በምዕራባዊው የዳር ድንበራችን ጉዳይ ላይ የማያሻማ አቋም መያዛችን የግድ ነው። ሱዳንና ህወሓት ለተስማሙበት የድንበር ወሰን ማጠየቂያቸው ግዌን የተባለ የእንግሊዝ ሻለቃ ሳለው የሚባለው መስመር መሆኑም አስቂኝ ነው። የሻለቃው ዋና ተግባር በአካባቢው የእንግሊዝን የቅኝ ግዛት ማስፋፋት እንጂ በካርቶሎጂ ሙያው ተመርጦ ወይም በእንግሊዝና በኢትዮጵያ የወቅቱ መንግስቶች ስምምነት የተሰየመ ህጋዊ ግለሰብ ያከናወነው ተግባር አይደለም። ሳለው የተባለውም ካርታ ለኢትዮጵያ መንግስት ቀርቦ የኢትዮጵያ መንግስትን ይሁንታ ያገኘ ሰነድ አልነበረም፣ አይደለም። ስለሆነም እንደ ህጋዊ ሰነድ ሊቀርብ አይችልም። ሁኔታው ህወሓት/ኢሕአዴግ በአልጀርስ ስምምነትና በኢትዮ-ኤርትራ የድንበር ኮሚሽን ፍርድ ቤት ላይ ሆን ብሎ ኢትዮጵያን ለመጉዳት ካሳየው ድርጊት ጋር ተመሳሳይ ከመሆኑም በላይ ዳግም ክህደት ነው። የአፍሪካ ሃገሮችን ድንበር በተመለከተ መሆን የሚገባው እንደ ፈረንጆች አቆጣጠር በ1963 ዓ/ም የጸደቀውን የአፍሪካ አንድነት ድርጅት ቻርተር ማክበር ነው። ቻርተሩ በቅኝ ግዛት ዘመን የነበሩት አገራዊ ድንበሮች መከበር እንዳለባቸው ያመለክታል። ምንም እንኳን በአካባቢው የሚኖሩ በርካታ ኢትዮጵያውያን የሱዳንና የኢትዮጵያ ድንበር ዛሬ በሱዳን ግዛት ስር ያሉትን ሰዋኪንና መዳኤን ቢያካትትም ቀደም ሲል በአጼ ኃይለ ሥላሴ ዘመን የተደረገው የድንበር ስምምነት መርጋት ይኖርበታል። ምክንያቱም ይህ የድንበር ስምምነት የአፍሪካ አንድነት ድርጅት ቻርተርን መሰረት ያደረገ መሆኑ ነው። በጉዳዩ ላይ በርካታ የኢትዮጵያ ታሪክ አዋቂዎችና የካርታ ጥበብ ባለሙያዎች ሃሳባቸውን እየሰጡበት የሚገኝ አገራዊ ጉዳይ ቢሆንም፥ የቅርቡ የሱዳንና የህወሓት የሚስጢር ስምምነት ኢትዮጵያን የሚጎዳና ምንም ዓይነት ህጋዊነትና የታሪክ ማስረጃ የሌለው የክህደት ውሳኔ ነው። ስለዚህም ኢሕአፓ (ዴ) የሚስጢር ስምምነቱን አጥብቆ ያወግዛል፥ በዚሁ የጠረፍ አካባቢ የሚኖሩ ጀግኖች ኢትዮጵያውያን ወገኖቻኘንን ጥረት ይደግፋል፥ ከጎናቸውም እንደሚሰለፍ ያረጋግጣል። መላው የኢትዮጵያ ሕዝብም በምዕራባዊው ጠረፎቻችን ካሉት ኢትዮጵያዊ እህቶቹና ወንድሞቹ ጋር እንደ አንድ ሕዝብ እንዲቆምና እንዲታገል ጥሪ ያቀርባል።

ቀደም ሲል የጠቅሰናቸውንና በኢትዮጵያ ላይ የተጋረጡትን ሦስት አደጋዎች ስናስብ የኢትዮጵያ የተቃዋሚ የፖለቲካ ኃይሎች የወቅቱ ሁኔታና ይዞታም ከፊታችን ይደቀናል። በኢትዮጵያ ውስጥ ያሉት የኤኮኖሚ የፖለቲካና የማኅበራዊ ኑሮ ሁኔታዎች በጣም አስከፊ ናቸው፥ እጅግ አስፈሪ ናቸው። እነኝህ አስከፊና አስፈሪ ሁኔታዎች ደግሞ ያለጥርጥር መቀየር አለባቸው፥ መወገድ አለባቸው። ለነዚህ አስከፊና አስፈሪ ሁኔታዎች መኖር ደግሞ ዋናው ተጠያቂ የህወሓት/ኢሕአዴግ ሃገርና ወገን ከሃዲ ቡድን ነው። አስከፊና አስፈሪ ሁኔታዎችን ለመለወጥና ለማስወገድ ህወሓት/ኢሕአዴግ የግድ መወገድ ይኖርበታል። ይህ

ተግባራዊ ሊሆን የሚችለው ደግሞ በተቃዋሚ የፖለቲካ ድርጅቶች ግንባር ቀደም ትግል ነው - የሕዝቡና የሌሎች ማኅበረሰባዊ ስብስቦች ብርቱ አስተዋጽዖ ሳይዘነጋና ሳይናቅ። ታዲያ የኢትዮጵያ የተቃዋሚ የፖለቲካ ኃይሎች እራሳቸውን ለዚህ አዘጋጅተዋልን? ይህንንስ ታላቅ ኃላፊነት ለመሸከም እንዲችሉ በሚያበቃቸው መንገድ ላይ እየተጓዙ ናቸውን?

እርግጥ ነው ዛሬ ብዙ ድርጅቶች ተከፋፍለዋል፥ ይህ ባይሆን ኖሮ ደግ ነበር። ነገር ግን ድርጅቶች ድርጅታዊ አንድነታቸውን ጠብቀው የተቀላጠፈና ፍሬያማ የፖለቲካ ስራ ለመስራት ሳይችሉ ቀርተው ለመለያየት ወይም ለመከፈል ሲበቁ ሊያስደነግጥና ተስፋ ሊያስቆርጥ አይገባም። ይልቁንም በሰለጠነና በጨዋ መንገድ የልዩነቶቻቸውን ምክንያቶችና ነጥቦች ያለማድበስበስ ለሚታገሉለት ሕዝብ ይፋ አድርገው በፍጥነት በሃገራዊና ሕዝባዊ ትግሉ ቀጣይነት ላይ ማትኮርና የየበኩላቸውን አዎንታዊ አስተዋጽዖ ማበርከት ይጠበቅባቸዋል። በሌላ መድረክ ሊገናኙ የሚችሉም ከሆነ የአንድነት ነጥቦችን አጥብቀው በመያዝ በፍሬያማ የፖለቲካና የማደራጀት ተግባራት ላይ ጊዜያቸውንና ኃይላቸውን ለማዋል መድከም ይኖርባቸዋል። በዛሬው የኢትዮጵያ ሁኔታ ተቃዋሚ የፖለቲካ ድርጅቶች መሰረታዊ እምነቶች በሆኑ ሦስት መሰረታዊ ጉዳዮች ላይ እስከተስማሙ ድረስ በአንዳንድ የአሰራርና ጥቃቅን ልዩነቶች ምክንያት እንደ ጠላት መተያዬት አይገባቸውም። ሦስቱ መሰረታዊ እምነቶችም (1) የኢትዮጵያ ግዛታዊ አንድነት የሕዝቧ ኅብረትና ብሄራዊ ሉዓላዊነት፤ (2) የዴሞክራሲያዊ ስርዓት እውን መሆንና የኢትዮጵያ ሕዝብ ሁለንተናዊ (የኤኮኖሚ የፖለቲካ የማኅበራዊና የሰብዓዊ) መብቶች ፍጹምነትና መከበር፤ (3) የህወሓት/ኢሕአዴግ ዘረኛና ከሃዲ አገዛዝ መወገድ ናቸው። በሦስቱ እምነቶች ላይ ስምምነት ከተደረሰ የሕዝባዊው ትግል ዋነኛ ደንቃራ ተወገደ፤ የጠንካራ ሕብረት መሰረት ተጣለ ለማለት ያስችላል ፥ የሕብረት ትግል ወቅታዊም ወሳኝም ነውና። ከሁሉም የፖለቲካ ድርጅቶች ወይም ኃይሎች አንዱ አንዱን ሊጎዱ ከሚችሉ ድርጊቶች ጨርሶ መቆጠብ ይጠበቅባቸዋል። በአሉታዊ ተግባሮች ተሸብቦ መቅረቱ ለድርጅትም ለሕዝብም የሚፈይደው እንደሌለ ካለፉት ዘመናት የትግል ታሪክ የመማር ዝግጁነት ሊኖር ይገባል። በዛሬይቱ ኢትዮጵያ በአሉታዊ ተግባራት ላይ ለሚሰማሩት የተቃዋሚ ድርጅቶች ቦታ ሊነፈጋቸው የሚገባ ለመሆኑም የጋራ ግንዛቤ እንዲኖር ይጠበቃል።

ብዙዎቹ የኢትዮጵያ ተቃዋሚ የፖለቲካ ድርጅቶች የአገሪቱ የፖለቲካ ችግሮች ያለ ድርጅቶች ኅብረት ሊቀረፍ የማይችል መሆኑንም የተገነዘቡ ይመስላል። ይህ ስሜትና የፖለቲካ ቅኝትም በአገር ውስጥና ከአገር ውጭ ባሉ በርካታ ድርጅቶች መሀል እየተንጸባረቀ መጥቷል። ይህ ደግሞ ለሕዝባችን ታላቅ የምስራች ነው። ኢትዮጵያ ከሁሉም ድርጅት በላይ ነች። ኢትዮጵያ ከማንኛው የፖለቲካ ግለሰብ በላይ ነች። ማንኛውም ድርጅት ሆነ የፖለቲካ ግለሰብ ሊኖርና ሊቀጥል የሚችለው ኢትዮጵያ ስትኖር ብቻ ነው። ኢትዮጵያ ደግሞ የምትኖረው ዳር ድንበሯ ሲጠበቅ፥ አገራዊ አንድነቷና ብሄራዊ ሉዓላዊነቷ ሲከበር፥ የሕዝቧ አንድነትና እኩልነት ሲረጋገጥ ነው። በዚህ የማያምንና ለተባበረ የፖለቲካ ትግል ራሱን ያላዘጋጀ ድርጅት ለወቅታዊው የሕዝባችን ትግል የሚፈይደው ምንም ነገር አይኖርም። ይልቁንም ፍላጎቱና ዓላማው ሊፈተሽ ይገባዋል። ያለጥርጥር ሃገርና ሕዝብን ባስቀደመ ኅብረት የህወሓት/ኢሕአዴግን አገዛዝ ማንኮታኮትና በከርሰ መቃብሩ ላይ ለኢትዮጵያ ሉዓላዊነትና የግዛት አንድነት መከበር እንዲሁም ለሕዝቧ እኩልነትና ማናቸውም ሙሉ መብት መረጋገጥ በተግባር የቆመ ዴሞክራሲያዊ ስርዓት በጋራ ለመገንባት መነሳት ይኖርብናል።

ድል ለኢትዮጵያ ሕዝብ!!
የኢትዮጵያ ግዛታዊ አንድነትና ብሄራዊ ሉዓላዊነት በሕዝቧ አንድነት ተከብሮ ይኖራል!!
ከሀዲውን ህወሓት/ኢሕአዴግን በኅብረት እንታገል!!